




**ዶ/ር አየለ የሸዋሉል**
**1926 - 2014**

# የዶ/ር አየለ የሸዋሉል አጭር የህይወት ታሪክ

ዶክተር አየለ የሸዋሉል ከአባታቸው ከግራዝማች የሸዋሉል መልከፀዲቅ እና ከእናታቸው ከወይዘሮ ይመኙሻል ዳምጠው በ1926 ዓ.ም. እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በአዲስ አበባ ከተማ ተወለዱ። እድሜአቸው ለትምህርት ሲደርስ በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ጨርሰዋል። ከዚያም የእርሻ ትምህርት ለመማር ወደ ዓለም ማያ ኮሊጅ ተመድበው ነበር። ሆኖም በአሜሪካኖች እርዳታ ሊቋቋም የታሰበው የእርሻ ኮሌጅ ግንባታ በወቅቱ ስላልደረሰ በጅማ የእርሻ ኮሌጅ ለሁለት አመታት እንዲሁም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሊጅ ለአንድ አመት ትምህርታቸውን ከተከታተሉ በኋላ ወደ ዓለማያ ኮሌጅ ተዘዋወረዋል። የዓለማያ ሲቋቋም በመጀመሪያ ከገቡት ተማሪዎች አንዱ ሲሆኑ በ1957 እ.ኤ.አ በከብት ጥበቃና እርባታ ትህምህርት (General Agriculture (BSc,) በባችለር ኦፍ ሳይንስ ዲግሪ ተመርቀዋል።

ከዚያም በከፍተኛ ትምህርት ከተመረቁት ሰወች አንዱ በመሆናቸው የእስኮላርሺፕ እድል ተሰጥቷቸው ወደ አሜሪካ በመሄድ በዩኒቨርስቲ ኦፍ ነብራስካ ትምህርታቸውን ተከታትለው እ.ኤ.አ በ 1959 ዓ.ም. በማስተርስ ዲግሪ (In Animal Husbandry & Pathology) ተመርቀው ወደ ሀገራቸው ተመልሰዋል።

ወደ ሀገራቸው ከተመለሱ በኋላ በመንግስት በተደረገላቸው የስራ ምደባ በጅማና በዓለማያ የእርሻ ኮሌጆች በመምህርነት ለተወሰኑ አመታት አገልግለዋል። ከዚያም ወደ እርሻ ሚኒስቴር ዋና መስሪያ ቤት ተዛውረው በከብት ጥበቃና እርባታ መምሪያ በኃላፊነት ቀጥሎም በግብርና ሚኒስቴር ምክትል ሚንስትርነት አገልግለዋል።

በአሜሪካና በኢትዮጵያ መንግስት ትብብር ልዩ የአመራር ብቃት ያሳዩ የመንግስት ኃላፊዎች እየተመረጡ ለልዩ ስልጠና አሜሪካ ይላኩ በነበረበት ወቅት ዶክተር አየለ የሸዋሉልም ተመርጠው ወደ አሜሪካ በመሄድ፣ በታወቀው የሀርቫርድ ዩኒቨርሲቲ በኬኔዲ ስኩል ኦፍ ገቨርንመንት (Harvard University Kennedy School of Government) ሁለተኛ ማስተርስ ዲግሪ በምጣኔ ሀብት እድገት እና በሕዝብ አስተዳደር (Masters of Degree in Economic Development & Public Administration) እ.ኤ.አ በ1970 ዓ.ም. ተመርቀዋል።

ወደ ሀገራቸው ተመልሰው የኢትዮጵያ የመጀመሪያውን የከብትና የሥጋ ቦርድ ድርጅትን በማቋቋም በሐላፊነት አገልግለዋል። ድርጅቱም በግብራናው ኢኮኖሚ ትልቅ ለውጥ ያሳየ ነበር።

በ1966 ዓ.ም በኢትዮጵያ ከተደረገው የመንግስት ለውጥ በኋላ ለዶክትሬት ዲግሪ ወደ ካናዳ ሄደው በ1983 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) ከዩኒቨርሲቲ ኦፍ ብሪቲሽ ኮሎምቢያ (University of British Colombia, Vancouver Canada (PHD) በዶክትሬት ተመርቀዋል። ከዚያም በተባበሩት መንግስታት የምግብና የእርሻ ድርጅት (United Nations Food & Agriculture Organization (FAO) የእርሻ አገልግሎቶችና ስልጠና ሲኒየር አማካሪ ( Agriculture extension, training & Education, special senior expert & consultant ) በመሆን ተቀጥረው በጣሊያን ሀገር በሮም ከተማ፣ በምስራቅ አፍሪካ፣ በምእራብ አፍሪካ፣ በደቡብ እስያ ፣በደቡብ አፍሪካ በተለያዩ ሀገሮችና በፓፓኒው ጊኒ ሰርተዋል።

ዶክተር አየለ የሸዋሉል በ (FAO) በስራ ላይ እያሉ ከወይዘሮ ይታይሽ ተገኘ ጋር እ.ኤ.አ በነሐሴ በ1989 ዓ.ም የሲቪል ጋብቻቸውን ውድ ባልንጀሮቻቸው፣ ወዳጆቻቸውና እህታቸው ወ/ሮ ሰብለወንጌል የሸዋሉል በተገኙበት በአሜሪካን ሀገር በዋሽንግተን ከተማ ፈፅመዋል። በመቀጠልም የቤተክርስቲያን ጋብቻቸውን በጥቅምት ወር 1989 አመተ ምህረት (እ.ኤ.አ) በቅዱስ ጳውሎስ የተባበሩት ቤተ ክርስቲያን (Saint Paul United Church of Canada) በ ስትራትፎርድ ኦንታሪዮ ከተማ የሚወዷቸው ዘመዶች ባልንጀሮችና ከተለያዩ ሀገራት የተጠሩ እንግዶች በተገኙበት ፈጽመው ኑሯቸውን ካናዳ አድረገው መኖር ጀመሩ።

ዶክተር አየለ የሸዋሉል ለዘመዶቻቸው፣ ለባልንጀሮቻቸው በተለይም ለሚወዷት ታናሽ እህታቸው ለወይዘሮ ሰብለወንጌል የሸዋሉልና ለባለቤታቸው ለፕሮፌሰር ደምሴ ሀብቴ በነበራቸው ከፍተኛ ፍቅርና የሀገር መውደድ ስሜት ፣ በየወቅቱ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት በጣም ጥሩ ጊዜ ያሳልፉ ነበር። ዶክተር አየለ የሸዋሉል በጣም በሚወዱት በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ሰንበቴ ማህበርም አባል ሆነው በደስታ፤ ይሳተፉ ነበር።

ዶክተር አየለ የሸዋሉል በአደረባቸው ህመም በቶሮንቶ ካናዳ በሚገኘው ሆስፒታል (University Health Network (UHN) ሲታከሙ ቆይተው የትዳር ጓደኛቸው ወይዘሮ ይታይሽ ተገኘ ከጎናቸው ሳይለዩ በኢትዮጵያውያን አቆጣጠር የካቲት 6, 2014 ዓ.ም. በተወለዱ በ87 ዓመታቸው ያለምንም ስቃይና ጣር በሰላም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።

## በጣም ለምወድህ የትዳር ጓደኛዬ !!

ፍቅረኛዬና ብቸኛ የቅርብ ጓደኛዬ፤ ራስህን ከፍ የማታደርግ፣ ለሰው ፍቅር የነበረህ፤ ኑሮው ላልተሳካለት፣ ፍትህ ለተጓደለበት ድምፅ የምትሆንላቸው ፣ እድል ፊቷን ላዞረችባቸው ለተራቡትና ለተጠሙት ተስፋ የምትሰጥ ነበርክ።

ውድ ባለቤቴ ከ33 ዓመት በላይ በትዳር ባሳለፍናቸው ዓመታት፣ ያሳለፍናቸው ደስተኛ ጊዜዎች ሳቆችና

ቀልዶች ከአእምሮዬ ለዘላለም አይጠፉም።

የትዳር ጓደኛዬ፣ መመኪያዬ፣ መኩሪያዬና የቅርብ ጓደኛዬ፣ በሥጋ ብለይህም በመንፈስ ሁልጊዜ በውስጤ ትኖራለህ። በህይዎቴ ላደረግህልኝ ታላቅ አስተዋጾና ላስተማርከኝ የህይወት ትምህርት እጅግ በጣም አመሰግናለሁ። አብረን ያቀድናቸውን አላማዎች በሙሉ በህይዎት እስካለሁ ድረስ ላሳካ ቃል እገባለሁ።

እስከ መጨረሻው እንደምዎድህ፣ እንደምኮራብህና እንደማከብርህ ቃል እየገባሁ በዚህ አለም ላለው ህይዎት እሰናበትሃለሁ።

ዶክተር አየለ የሸዋሉል ወደ ሀገራቸው ኢትዮጵያ ሄደው ለመቀበር በተመኙት መሰረት የቤተሰባቸው መቃብር በሚገኝበት በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በዛሬው ዕለት ተፈፅሟል።

ለባለቤታቸው፣ ለእህታቸው ባል፣ ለእህትና ወንድሞቻቸው ልጆች፣ ለዘመዶቻቸውና ለወዳጆቻቸው እግዚአብሄር ጽናቱን እንዲሰጣቸው እንጸልያለን።

በቀብር ስነ ስርዓቱ ላይ የተገኛችሁት በሙሉ በስማቸው የተዘጋጀውን ጸበል ጸዲቅ በሰንበቴው አዳራሽ ተገኝታችሁ የበረከቱ ተካፋይ እንድትሆኑ በአክብሮት እንጋብዛለን።

እናመሰግናለን።
ባለቤታቸው ወይዘሮ ይታይሽ ተገኝ
ፕሮፌሰር ደምሴ ሃብቴ /ዋርሳ/
የእህትና የወንድም ልጆች
ዘመዶቻቸውና ባልንጀሮቻቸው
የሰንበቴ ማህበርተኞች
የቅዱስ ጊዮርጊስ ካህናት